| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ግጥም ፤ "ከመቃብር ፡ በላይ" ፡ ዐምድ ። |
| ርእስ ፤ | "ለሲዳሞ ፡ ጮራ ። " |
| ደራሲ ፤ | አክሎግ ፡ ዘለቀ ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1962 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2018-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልታተመ ። ) |

# ከመቃብር ፡ በላይ ።

## ለሲዳሞ ፡ ጮራ ።

### አክሎግ ፡ ዘለቀ ።

(ደራሲው ፡ አክሎግ ፡ ዘለቀ ፡ ይህን ፡ ግጥም ፡ የደረሱት ፡ ሚያዝያ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1962 ፡ ዓ.ም. ፥ በሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ነዋሪ ፡ ኾነው ፥ የሌ.. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴን ፡ ባዲስ ፡ አገረ ፡ ገዢነት ፡ ወደ ፡ ሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ መምጣትን ፡ ሰምተው ፥ ባንድ ፡ ወገን ፥ ሲያብገነግናቸው ፡ የኖረውን ፡ በወቅቱ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የታዘቡትን ፡ የሥልጣን ፡ ብልግና ፡ ለመክሠት ፥ በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፥ ያዲሱ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ማንነት ፡ እና ፡ ዝና ፡ የፈጠረባቸውን ፡ ተስፋ ፡ ከማስጠንቀቂያ ፡ ጋራ ፡ ለመግለጽ ፡ ነበር ።

ከሥነ ፡ ጽሑፋዊ ፡ ዋጋው ፡ ሌላ ፥ የግጥሙ ፡ ሙሉ ፡ ቅጂ ፡ እዚህ ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ የወጣበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፥ በዚሁ ፡ የሥልጡንሕዝብና ፡ ቍ.2018-003 ፡ ዕትም ፥ በ"ሐተታ ፡ መጻሕፍት" ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ የደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡ "ሕይወቴ ። " ፡ የተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ሐተታ ፡ ውስጥ ፡ በከፊል ፡ ተጠቅሶ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ሙሉው ፡ ድርሰት ፡ በዚህኛው ፡ ዐምድ ፡ ቢወጣ ፡ በወቅቱ ፡ የነበረውን ፡ ኹኔታ ፡ ፍንትው ፡ አድርጎ ፡ የሚያስገነዝብ ፡ ታሪካዊ ፡ ሰነድ ፡ ስለሚኾን ፡ ነው ። )

---

እየነጋ ፡ ሲኼድ ፥ ሥራው ፡ እያበራ ፥
በእየደረሰበት ፡ ሀገሩን ፡ ሲያኰራ ፥
ዕድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ እንዲሁ ፡ በተራ ፥
ብቅ ፡ ዐለ ፡ በደቡብ ፡ ለሲዳሞ ፡ ጮራ ።

ለምለሙ ፡ ሲዳሞ ፥ እንኳን ፡ ደስ ፡ ዐለኽ!
ጨልሞብኽ ፡ ነበር ፥ አኹን ፡ ነጋልኽ ።
እስካኹን ፡ ሲዳሞ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ የኾንከው ፧
ኑሮኽ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፧ እኔ ፡ ነኝ ፡ የማውቀው ።
ለምን ፡ እኔ ፡ ብቻ ፧ ማንም ፡ ይመስክር ፥
እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያንተ ፡ አስተዳደር ።
በክፍል ፡ በክፍሉ ፥ በእየተዋረደ ፥
በብዙ ፡ ሺሕ ፡ ገንዘብ ፥ በብዙ ፡ ፓውንድ ፥
ኮንትራት ፡ ተሰጥተኽ ፡ እንደራስ ፡ ሑዳድ ፥
አምርተኽ ፡ አትበላ ፥ አስብተኽ ፡ አታርድ ፥
ዳኝነት ፡ ተነፍገኽ ፡ ኑሮኽ ፡ ሥር ፡ በግድ ።

እየነጋ ፡ ሲኼድ ፥ ሥራው ፡ እያበራ ፥
በእየደረሰበት ፡ ሀገሩን ፡ ሲያኰራ ፥
ዕድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ እንዲሁ ፡ በተራ ፥
ብቅ ፡ ዐለ ፡ በደቡብ ፡ ለሲዳሞ ፡ ጮራ ።

ሌ/ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፥
ለደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲኾኑ ፡ እንደራሴ ፥
ሕዝቡ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ፍጥረታቱ ፡ ኹሉ ፡
በእውነት ፡ ይገባል ፡ ዕሠይ! ፡ እልል! ፡ ሊሉ ።
ታላቁ ፡ ጌታዬ ፥ ክቡር ፡ ጄኔራል ፥
እንኳን ፡ ደስ ፡ አለዎ ፡ ለርስዎ ፡ እንዳልል ፥
ዐዲሱ ፡ ደረጃ ፣ ዐዲሱ ፡ ሥልጣን ፥
እንደ ፡ ችሎታዎ ፣ ድካምዎ ፡ መጠን ፥
ስለ ፡ መሰለኝ ፡ ነው ፡ የማይመጣጠን ።
ቢኾንም ፥ ሲዳሞ ፡ ነጻነት ፡ አግኝቷል ፤
ከተናጣቂ ፡ አውሬ ፡ ከተኰላዎች ፡ ድኗል ።
ኸረ ፡ ለጃንሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጣቸው ፤
ሲዳሞን ፡ ከተኰላ ፣ ካውሬ ፡ ማዳናቸው ።

እየነጋ ፡ ሲኼድ ፥ ሥራው ፡ እያበራ ፥
በእየደረሰበት ፡ ሀገሩን ፡ ሲያኰራ ፥
ዕድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ እንዲሁ ፡ በተራ ፥
ብቅ ፡ ዐለ ፡ በደቡብ ፡ ለሲዳሞ ፡ ጮራ ።

እንግዲህ ፡ ጌታዬ ፥ ጄኔራል ፡ ጐበዙ ፥
በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲዳሞን ፡ ሲገዙ ፥
ዐደራ ፡ የምለው ፡ ይኖረኛል ፡ ብዙ ።
አንተን ፡ ምን ፡ አገባኽ ! ዐደራው ፡ ምንድን ፡ ነው ?
ደግሞስ ፡ ለምንድን ፡ ነው ፡ የምትቀባጥረው ?
የተባልኩ ፡ እንደኾን ፡ እኔን ፡ ያገባኛል ፤
የትውልዴን ፡ ሐረግ ፡ ስስብ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።
ኀይለ-ሥላሴ ፡ እና ፡ ገነተ-ማርያም ፥
ያንድ ፡ አንገፍት ፡ ልጅ ፡ ናቸው ፥ እት ፡ እና ፡ ወንድም ።


©አ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

እኔ ፡ የገነት ፡ ልጅ ፥ ክቡርነታቸው ፡
የኀይለ-ሥላሴ ፥ ያንጋፋው ፡ ልጅ ፡ ናቸው ።
ከታላቅ ፡ ከታናሽ ፥ ካንድ ፡ የተወለዱ ፥
ምን ፡ እና ፡ ምን ፡ ናቸው ፤ እናንተው ፡ ፍረዱ ።
ራሴ ፡ ስላለኹ ፡ በዚያ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፥
ተጥዬ ፡ እንደ ፡ ጒድፍ ፥ ርስቴን ፡ በማቅናት ፤
መልካሙ ፡ ዝናዎ ፥ ጥንት ፡ የታወቀው ፥
ሲታማ ፡ ብሰማ ፡ በእያንዳንድ ፡ ሰው ፥
ዝም ፡ ብዬ ፡ ለማለፍ ፡ እንዳልሰማ ፡ ሰው ፥
የኔ ፡ አንገት ፡ አይችልም ፥ ሆደ ፡ ባሻ ፡ ነው ።

እየነጋ ፡ ሲኼድ ፥ ሥራው ፡ እያበራ ፥
በእየደረሰበት ፡ ሀገሩን ፡ ሲያኰራ ፥
ዕድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ እንዲሁ ፡ በተራ ፥
ብቅ ፡ ዐለ ፡ በደቡብ ፡ ለሲዳሞ ፡ ጮራ ።

ስለዚህ ፥ ክቡር ፡ ሆይ ! የማስታውሰው ፥
እንደተረዳኹት ፥ እኔ ፡ እንደማውቀው ፥
ብዙ ፡ ሐተታ ፡ አለው ፡ የሲዳሞ ፡ ሰው ።
በሥራ ፡ ላይ ፡ ካሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፥
ከተጠሪ ፡ ቀሮ ፣ ከባላባቶች ፥
ዐራሽ ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ከገበሬዎች ፥
ፍጹም ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ከነጋዴዎች ፥
ከሰባ ፡ ሰማንያ ፥ ከመቶ ፡ የማይበልጡ ፥
እንደ ፡ ቄላ ፡ ትኋን ፡ ደምን ፡ የሚመጥጡ ፥
በነፍስ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ገንዘብ ፡ እያዋጡ ፥
በጭንነት ፡ ይቀርባል ፡ ገገሮዎች ፡ ሲመጡ ።
የደንቡ ፡ ሲፈጸም ፡ በእየማኅበሩ ፥
ዐምባ-ገነን ፡ ኹነው ፡ ኹሉም ፡ በእየበሩ ፥
ሕዝቡን ፡ የገፉታል ፡ እየተባበሩ ።
ገኘሮውም ፡ በንዋይ ፡ ስለ ፡ ተገሠተተ ፥
ዐይኑን ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እያንከራተተ ፥
መሣሪያቸው ፡ ሲኾን ፡ ላገር ፡ ዘራፊዎች ፥
ደግ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚመች ?

እየነጋ ፡ ሲኼድ ፥ ሥራው ፡ እያበራ ፥
በእየደረሰበት ፡ ሀገሩን ፡ ሲያኰራ ፥
ዕድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ እንዲሁ ፡ በተራ ፥
ብቅ ፡ ዐለ ፡ በደቡብ ፡ ለሲዳሞ ፡ ጮራ ።

ይሄ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ መዐት ፡ ነው ፡ መዘዙ ፤
ሕዝቡን ፡ በክሎታል ፡ የክፉ ፡ ሰው ፡ መርዙ ።
በጣም ፡ ታስቦበት ፥ ሌት ፡ ተቀን ፡ ተመክሮ ፥
እንደወባ ፡ ማጥፊያ ፡ እንዳንበጣ ፡ ቢሮ ፥
የጒቦ ፡ ማውደሚያ ፡ በሚል ፡ ተሠይሞ ፥
ድርጅት ፡ ካልቆመ ፡ አይድንም ፡ ሲዳሞ ።
ሌላው ፡ ኹሉ ፡ ቀርቶ ፥ በእኔ ፡ አስተያየት ፥
ይህን ፡ ማጥፋት ፡ ነው ፡ ትልቁ ፡ ልማት ።
እዝርዝር ፡ ሳልገባ ፥ እንዲያው ፡ በደፈናው ፥
ስለ ፡ ማናለብሽ ፡ ጌታዬን ፡ የምለው ፥
ስለ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ብዬ ፡ የምደውለው ፥
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከቅርብም ፡ ከሩቁ ፥
ስምዎን ፡ ጠብቀው ፡ እንደ ፡ አልማዝ ፡ እንደ ፡ ዕንቍ ፥
ዛሬ ፡ እንዳይበላሽ ፡ ጌታዬ ፡ ይጠንቀቁ ፤
ባገሩ ፡ መኖሬን ፡ እንሆ ፡ እያወቁ ፥
እኔንም ፡ ድኻዎን ፡ እንዳያሣቅቁ ።
በማዕረግ ፡ በሥልጣን ፡ ታላቅ ፡ ጄኔራል ፤
በሀብትም ፡ እንደኾን ፥ ያለው ፡ ይበቃል ፤
ለስም ፡ ብቻ ፡ መጣር ፣ ማሰብ ፡ ይገባል ።
ባጠፋም ፡ ይቅርታ ፡ ይማሩኝ ፡ ጌታዬ ፤
ጫማዎን ፡ በመሳም ፡ አለኝታዬ ፡ ብዬ ፥
እንግዲህ ፡ ኼጃለኹ ፡ ከድኻ ፡ ጒዠዬ ።

እየነጋ ፡ ሲኼድ ፥ ሥራው ፡ እያበራ ፥
በእየደረሰበት ፡ ሀገሩን ፡ ሲያኰራ ፥
ዕድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ እንዲሁ ፡ በተራ ፥
ብቅ ፡ ዐለ ፡ በደቡብ ፡ ለሲዳሞ ፡ ጮራ ።

የሩቅ ፡ ተቈርቋሪ ፡ ወገንዎ ፡ ነኝ ፤
አክሎግ ፡ ዘለቀ ፤
ሚያዝያ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1962 ፡ ዓ.ም. ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።